# Healthy smiles Ontario

## ነፃ የጥርስ ህክምና መርሃግብር እድሜአቸው 17 አመትና ከዚያ በታች ለሆኑ ልጆች

**Healthy Smiles Ontario ምንድን ነው?**
Healthy Smiles Ontario ምንም አይነት የጥርስ ህክምና ሽፋን ለማያገኙ እድሜአቸው 17 ዓመት እና ከዚያ በታች ለሆኑ ልጆች የሚሆን አዲስ መርሃግብር ነው፡፡ መስፈርቱን የሚያሟሉ ከሆነ፣ ልጆችዎ ያለ ምንም ክፍያ መደበኛ የጥርስ ህክምና አገልግሎት ያገኛሉ፡፡

**መስፈርቱን የሚያሟላ ማን ነው?**
እድሜአቸው 17 ዓመት እና ከዚያ በታች የሆኑ ልጆች መስፈርቱን የሚከተሉት፤

- የኦንትሪዮ ነዋሪዎች ከሆኑ ፣
- የቤተሰባቸው የተጣራ ዓመታዊ ገቢ $20,000 ወይም ከዛ በታች ከሆነ፣ እና
- የማንኛውም አይነት የጥርስ ህክምና ሽፋን ከሌላቸው (እንደ ኦንትሪዮ ስራዎች ያለ ሌሎች መንግስት የሚደግፉቸው መርሃግብሮችንም ጨማሮ)

መስፈርቱን ለማሟላት ስለሚያስፈልጉ ነገሮች የበለጠ ለማወቅ እንዲሁም ስለ Healthy smiles Ontario እና መስፈርቱን ለማሟላትዎ ለማረጋገጥ ስለሚያስፈልጉ ሰነዶች ለማወቅ ሰርቪስ ኦንትሪዮ ኢንፎላይን ከክፍያ ነጻ በስልክ ቁጥር 1-866-532-3161 (TTY toll-free at 1-800-387-5559) ይደውሉ ወይም በአካባቢያዎ ያለን የህዝብ ጤና ክፍልን ያነጋግሩ፡፡ የህዝብ ጤና ክፍሎች ዝርዝር በ ontario.ca/healthysmiles ሊገኝ ይችላል፡፡

**እንዴት ማመልከት እችላለሁ ?**
ለማመልከት በአካባቢዎ ያለን የህዝብ የጤና ክፍል ማነጋገር ያስፈልግዎታል፡፡ የርስዎ የህዝብ ክፍል በማመልከቻዎ ሂደት፣ ማለትም ይህንን ቅፅ በመሙላትንና አስፈላጊ ሰነዶችን በማሳየት፣ ይረዱዎታል።

**ምን አይነት አገልግሎቶች ነው የሚሸፈነው?**

- ፈቃድ ባለው የጥርስ ህክምና ሰጭ ጋር መደበኛ ጉብኝት፣ እንደ የጥርስ ሃኪም እና የጥርስ ጽዳት ባለሞያ ያሉ
- ማጽዳት
- መሙላት
- ኤክስ-ሬይ
- አዲስ ጥርስ መትከል
- እና ሌሎችም

**ሽፋን የሌላቸው አገልግሎቶች ምንድን ናቸው?**

- ጥርስን የማስዋብ፣ እንደ ጥርስ ማንጣት የመሳሰሉ
- ኦርቶዴንቲክስ፣ እንደ ብሬስ ያለ
- ድንገተኛ የአፍ የጤና እንክብካቤ

እድሜው 17 እና ከአስራሰባት ዓመት ያልሞለው ልጅ ድንገተኛ የአፍ ጤና ጉዳይ ቢገጥመው፣ አገልግሎቱ እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸው ህፃናት (CINOT) መርሃግብር ስር ሊሸፈን ይችላል፡፡ እባክዎን የበለጠ ለማወቅ በአካባቢያዎ ያለን የህዝብ ጤና ክፍልን ያነጋግሩ ወይም ontario.ca/cinot ይሂዱ፡፡

**ልጄ እንደ ጤናማ ፈገግታዎች ኦንትሪዮ የጥርስ እንክብካቤ የት ነው ማግኘት የሚችለው?**
አንድ ጊዜ የማመልከቻው ሂደት ከተጠናቀቀ፣ በአካባቢዎ ያለ የህዝብ የጤና ክፍል በማህበረሰብዎ ውስጥ ያሉትን አማራጭ የጥርስ ህክምና አገልግሎቶች ያሳውቅዎታል፡፡ ይህም እርስዎ እንደሚኖሩበት አካባቢ የግል የጥርስ ህክምና ሰጭዎችን እና/ወይም የህዝብ የጤና ክፍል ወይም የማህበረሰብ የጥርስ ህክምና ክሊኒክን ሊያጠቃልል ይችላል፡፡

**ልጄ የእኔ የጥርስ ሃኪም ጋር መታከም ይችላል?**
ልጅዎ Healthy Smiles Ontario መርሃግብር ውስጥ እየተሳተፈ ከሆነ የእርስዎ የጥርስ ሃኪም ጋር መታከሙን መቀጠል ይችላል፡፡ የጥርስ ሃኪምዎ መርሃግብሩ ውስጥ የማይሳተፍ ከሆነ፣ በዚህ መርሃግብር ውስጥ እየተሳተፉ እንደሆነ ለማወቅ በአካባቢዎ ያለ ሌላ የጥርስ ሃኪም ወይም የጥርስ ጽዳት ባለሞያ ማግኘት ይችላሉ፡፡

Ontario

Catalogue No. 015169 October 2010 "Healthy Smiles Ontario" Amharic-Ethiopian © 2010 Queen's Printer of Ontario